# **“ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለኅብረብሔራዊ አንድነት”**



የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት መከበር ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ያረጋገጠው የኢፌዲሪ ሕገመንግስት የጸደቀበትን ቀን ህዳር 29 በየዓመቱ በተለያዩ ሁነቶች ላለፉት 19 ዓመታት ሲከበር ቆይቷል።

´በ2018 ዓ.ም ለ20ኛ ጊዜ "**ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለኅብረብሔራዊ አንድነት**" በሚል መሪ ቃል ይከበራል።

´በመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ፖሊሲ እንዲሁም ፖሊሲውን መሰረት አድርጎ በመተግበር ላይ የሚገኘው ግዙፍ አገራዊ ሪፎርም ብዝሃነትና አካታችነትን ያረጋገጠ ሲቪል ሰርቪስ መገንባት የሚለውን ጉዳይ እንደ አንድ አምድ ተለይቶ ይህንንም ለማስተግበር በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

´በዚህ ሪፎርም ብዝሃነትና አካታችነት የሴቶችን፣ ወጣቶችንና አካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ማረጋገጥና የብሄሮችን ተካታችነት ማጎልበት ዋና ጉዳይ በማድረግ ለማስተግበር በርካታ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።

´የዘንድሮው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ሲከበር የመንግስት ሰራተኛው በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ እንዲጎለብት የሚፈለገውን የብዝሃነትና አካታችነት ጉዳይ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል በመውያየት መሆን ይኖርበታል።

ምክንያቱም ህብረብሄራዊ አንድነት እውን የሚሆንበት አንዱ መንገድ ለብዝሃነት እውቅና የሰጡና አካታች ተቋማትን በመፍጠር ስለሆነ ነው።

´በመሆኑም “ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለኅብረብሔራዊ አንድነት” የሚለውን መሪ ቃል ብዝሃነትና አካታችነትን ያረጋገጠ ሲቪል ሰርቪስ ከመገንባት ጋር አስተሳስሮ መመልከት ተገቢ ይሆናል።

## የብዝሃነት እና አካታችነት ጽንሰ-ሃሳብ

´ብዝሃነት ሲባል በተቋም ውስጥ በሰዎች መካከል ያለ የፆታ፣ የዕድሜ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የብሄር እና የመሳሰሉ ባህሪያት ልዩነትን የሚያመለክት ነው።

´ብዝሃነትን አቃፊ መሆን ማለት እነዚህን ልዩነቶች አክብሮ ተገቢውን እውቅናና ዋጋ ሰጥቶ በአግባቡ ማስተናገድ ነው።

´ብዝሃነት ለተቋማት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ብዝሃነት ፈጠራንና ትብብርን በማበረታታት ጠንካራና አካታች የሥራ አካባቢን ለመፍጠር አስፈላጊ ነው።

´ለብዝሃነት እውቅና የሰጡ ተቋማት ከበርካታ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች ተጠቃሚ ስለሚሆኑ የተሻለ ውሳኔ የመስጠትና ችግሮችን የመፍታት አቅም አላቸው።

´ብዝሃነት ከሁሉም የማህበረሰብ ዳራ የመጡ ግለሰቦች ዓላማቸውን እንዲያሳኩ እድል በመስጠት የበለጠ ፍትሃዊነትን እና ፍትሃዊ ማህበረሰብና ተቋምን ለመፍጠር ይረዳል።

´ብዝሃነትን ያረጋገጡ ተቋማት ፈጠራ፣ ጥሩ የችግር አፈታት ልምድ፣ ውሳኔ የመስጠት አቅም፣ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በቀላሉ የመላመድ ብቃት፣ የተገነባ የሠራተኞች ሞራል፣ በሥራ ላይ የመቆየት ፍላጎት ያላቸው ሠራተኞች፣ የተሻለ የሥራ አፈጻጸም እና ተደራሽነት አላቸው።

´´ከዚህ በተቃራኒው ብዝሃነት በሌለባቸው ተቋማት ውስጥ ውስን አመለካከቶች፣ ውስን ተደራሽነት፣ የተለያዩ ተሰጥኦዎች ያሏቸው ሠራተኞችን ለመሳብና ለማቆየት አለመቻል፣ መልካም ያልሆነ ተቋማዊ ስም እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችን መጠቀም አለመቻል ሰፍነው ይታያሉ።

´አካታችነት ከብዝሃነት ጋር ጎን ለጎን መታየት የሚገባው ጽንሰ-ሃሳብ ነው።

´አካታችነት ሁሉም ሰዎች ዋጋ ያላቸው እና የተከበሩ በመሆናቸው ልዩ የሚያደርጓቸውን ባህሪያት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በማንኛውም ተቋማዊ ጉዳይ ተሳታፊ የሚያደርግ የሥራ አካባቢ መፍጠር ነው።

´በተጨማሪም አካታችነት ልዩነትን ማወቅ፣ መቀበልና ሁሉም ሰዎች የዕድሎችና ሃብቶች እኩል ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ በትጋት መስራትን ያካትታል። አካታችነት ግለሰቦች እራሳቸውን እንዲሆኑና ልዩ አመለካከታቸውንና ልምዶቻቸውን እንዲገልጹ የሚበረታቱበትን ሁኔታ የመቀበልና የመረዳት ባህል ማሳደግን ይጨምራል።

´በተቋማት ውስጥ አካታችነትን ማሳካት የሚቻለው ፍትሃዊነትን እና ማካተትን በሚያበረታቱ ፖሊሲዎችና የአሰራር ስርዓቶች አማካኝነት ነው።

´በመሆኑም አካታችነትን በማስተዋወቅ ሠራተኞቻቸው የተሻለ የሥራ ውጤት እንዲያበረክቱና ሙሉ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ ተቋማት የበለጠ አወንታዊና ውጤታማ የሥራ አካባቢ መፍጠር ይችላሉ።

´ምክንያቱም አካታችነት እንቅፋቶችን በማስወገድና ማህበራዊ ፍትህን በማጎልበት ሁሉም ግለሰቦች በተቋማት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ እድል ለመፍጠር ስለሚያስችል ነው።

´አካታች የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የመጀመሪያው እርምጃ ለብዝሃነት እውቅና መስጠት ነው።

´

ያለብዝሃነት አካታችነት ሊኖር ስለማይችል ብዝሃነትን መረዳትና እውቅና መስጠት ያስፈልጋል።

´አካታችነት የልዩነት መገለጫዎችን መሰረት ያደረጉ አድሎዎች፣ ፍረጃዎችና መለያየቶች በተቋማትም ሆነ በማህበረሰብ ውስጥ እንዳያድጉ እና በሰዎች መካከል ያለው የስነ-ልቦናዊ ትስስር እንዳይላላ የሚከላከል እንዲሁም ለብዝሃነት መከበር፣ እውቅና ማግኘትና መቻቻል መጎልበት መሰረት የሚጥል ነው።

´በአጠቃላይ በብዝሃነትና አካታችነት አተገባበር ውስጥ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሊፈጸሙ የሚችሉ አድሎአዊ አሰራሮችን መለየትና መቆጣጠር ያስፈልጋል።

´ምክንያቱም አካታችነትና ብዝሃነት "ያገባኛል ባይነት እና ልዩ ማንነት አለኝ ይህም ይታወቅልኝ" ባይነት እንደመሆኑ ሠራተኞች በተግባር የተካታችነት ስሜት ካጎለበቱ ከነሙሉ ማንነታቸው ወደ ተቋሙ በአካልና በአእምሮ መምጣት ይችላሉ።

´በተጨማሪም በነፃና በግልፅ ሁኔታ ሃሳባቸውን መግለጽ፣ ችግሮቻቸውን መፍታት፣ በፈጠራ፣ በአፈጻጸም ማሻሻያ ሂደቶች ውስጥ በብዙ መልኩ መሳተፍና ውጤት ማስመዝገብ ይችላሉ።

´እንደ አገር የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ስናከብር በየመስሪያ ቤታችን ያለውን የብሄር ብዝሃነትና አካአታችነት በመገምገምና በዚህ ረገድ ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ጉዳዮች በመወያየት ሊሆን ይገባል።

´ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አገር ናት።

´በህገ-መንግስቱ መሰረት ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ-ልበና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው።

በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት በሁሉም ሰዎች መካከል ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ ፊት እኩል ጥበቃ እንደሚደረግላቸው፤ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በኃይል፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት እንዳላቸው ተደንግጓል።

´በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 በብሔር፣ በጾታ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ ሁኔታ በሥራ ፈላጊዎችም ሆነ በመንግስት ሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ተግባር እንደሆነ ተደንግጓል።

´በዚህ አዋጅ ብዝኃነትና አካታችነት እና ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃ አፈፃፀምን አስመልክቶ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ብሄሮች ሊጠበቁ የሚገቡ የሥራ ሁኔታዎችንና የተጨማሪ ድጋፍ እርምጃ ተጠቃሚነት መብቶችን ዘርዝሮ አስቀምጧል።

´እነዚህ በህግ ማዕቀፍ የተቀመጡት የብዝሃነትና የአካታችነት ድንጋጌዎች የኢትዮጵያ መንግስት ሠራተኞችና ተቋማት ብዝሀነትንና አካታችነትን በህግ ለመምራት የተሄደበትን ርቀት የሚያመላክት ጉዳይ ነው። ´በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 በብሔር፣ በጾታ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ ሁኔታ በሥራ ፈላጊዎችም ሆነ በመንግስት ሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ተግባር እንደሆነ ተደንግጓል።

በዚህ አዋጅ ብዝኃነትና አካታችነት እና ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃ አፈፃፀምን አስመልክቶ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ብሄሮች ሊጠበቁ የሚገቡ የሥራ ሁኔታዎችንና የተጨማሪ ድጋፍ እርምጃ ተጠቃሚነት መብቶችን ዘርዝሮ አስቀምጧል።

´እነዚህ በህግ ማዕቀፍ የተቀመጡት የብዝሃነትና የአካታችነት ድንጋጌዎች የኢትዮጵያ መንግስት ሠራተኞችና ተቋማት ብዝሀነትንና አካታችነትን በህግ ለመምራት የተሄደበትን ርቀት የሚያመላክት ጉዳይ ነው።

´ህዳር 29 ቀን 2018 ዓ.ም ለ20ኛ ጊዜ "ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለኅብረብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ስናከብር ወደሚጨበጥ ተስፋ የምንቀይርበት አንዱ መንገድ የተጀመረውን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም (በተለይ ብዝሃነትና አካታችነትን ያረጋገጠ ስርዓት) ተግብሮ በማሳየት ነው።

´በመሆኑም ቀድመው ወደ ሪፎርሙ የገቡም ሆነ በቅርቡ የሚገቡ የመንግስት ተቋማት የተዘጋጁ የፖሊሲና የህግ ማእቀፎችን ከብዝሃነትና አካታችነት አኳያ በመቃኘት ተቋማዊ ለውጡ አገራዊ ፋይዳ በሚፈጥር አግባብ መተግበር ይጠበቅባቸዋል።

**በኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ**

**ህዳር 2018 ዓ.ም**